# G-SC[H19-67 C]

# የመጀመሪያው አጋማሽ የ6ኛ ክፍል ሒሳብ ሞዴል ፈተና

የጥያቄ ብዛት 30

የተፈቀደ ስዓት 1 ስዓት

ስም________________________________ ክፍል________ቁጥር_______

## ፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛ መልስ የያውን ፊደል ብቻ ምረጡ::

1. በ246 እና በ253 መካከል ስንት ኢ-ተጋማሽ መሉ ቁጥሮች አሉ?

ሀ. 3 ለ. 5 ሐ. 6 መ. 4

2. 9 $\frac{4}{13}$ ወደ ህገወጥ ክፍልፋይ ሲለወጥ _______ይሆናል::

ሀ. $\frac{117}{13}$ ለ. $\frac{121}{13}$ ሐ. $\frac{48}{13}$ መ. $\frac{113}{13}$

3. ከሚከተሉት ውስጥ ተተንታኝ የሆነው ሙሉ ቁጥር የቱ ነው?

ሀ. 2 ለ. 29 ሐ. 51 መ. 71

4. $\frac{78}{60}$ በዝቅተኛ ሒሳባዊ ቃል ሲገለፅ _________ ይሆናል::

ሀ. $\frac{39}{40}$ ለ. $\frac{13}{8}$ ሐ. $\frac{13}{10}$ መ . $\frac{39}{10}$

5. ከሚከተሉት ውስጥ የ69 አካፋይ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. 17 ለ. 21 ሐ. 3 መ. 1

6. የ200 እና 120 ትንሹ የጋራ ብዜት ስንት ነው?

ሀ. 120 ለ. 200 ሐ. 400 መ. 600

7. 4 $\frac{3}{5}$ % ወደ አስርዮሽ ቁጥር ሲቀየር _______ ይሆናል::

ሀ. 4.6 ለ. 0.6 ሐ. 0.06 መ. 0.046



LIVEWORKSHEETS

8. ሙሉ ቁጥር 4,23ሀ ፣ በ'ሀ' ቦታ በመተካት ለ4 ተካፋይ የሚያደርገው ቁጥር የቱ ነው?

ሀ. 0 ለ. 4 ሐ. 6 መ. 3

9. 3.06+ $2\frac{1}{4}$ =_________

ሀ. 3 $\frac{3}{8}$ ለ. 5.31 ሐ. 5 $\frac{1}{4}$ መ. 3.71

10. የ1 ቤት ሆሄያቸው በ '0' የሚጨርሱ ሙሉ ቁጥሮች ሁሉ ተካፋይ የማይሆኑት ለየትኛው ነው?

ሀ. 5 ለ. 10 ሐ. 2 መ. 4

11. $\frac{16}{24}$ ወደ መቶኛ ሲለወጥ________ ነው።

ሀ. 66% ለ. 0.6' % ሐ. 66.6' % መ. 16%

12. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. 0.3< $\frac{2}{5}$ < $2\frac{1}{4}$ < 90% ሐ. 90%> 0.3 > 2 $\frac{1}{4}$ > $\frac{2}{5}$

ለ. 0.3 < $\frac{2}{5}$ < 90%< 2 $\frac{1}{4}$ መ. $2\frac{1}{4}$ > 90% > 0.3 > $\frac{2}{5}$

13. የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ትጋብ እና ትጋአ በቅደም ተከተል 150 እና 5 ነው። ከሁለቱ ቁጥሮች ውስጥ አንዱ 15 ቢሆን ሁለተኛው ቁጥር ስንት ነው?

ሀ. 720 ለ. 75 ሐ. 5 መ. 50

14. $\frac{180}{60}$= $\frac{\square}{5}$ የ'ወ' ዋጋ ስንት ነው?

ሀ. 15 ለ. 18 ሐ. 60 መ. 10

15. 140 በብቸኛ ትንትኑ _________ ነው።

ሀ. $2 \times 3^2 \times 7$ ለ. $2^2 \times 5 \times 7$ ሐ. $2^3 \times 3^2 \times 5$ መ. $2 \times 5^2 \times 7$

16. $\frac{1}{50}$ በአስርዮሻዊ ቁጥር ሲገለፅ _______ ይሆናል።

ሀ. 0.2 ለ. 2.4 ሐ. 0.02 መ. 0.1



LIVEWORKSHEETS

17. ት.ጋ.አ(88፣128)=________

ሀ. 64 ለ. 88 ሐ. 8 መ. 1,408

18. በሐምሌ 19/67 ት/ቤት ውስጥ በ2016ዓ.ም በ6 ሴት እና 4 ወንድ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል የመጀመሪያ ዙር ጥያቄና መልስ ውድድር ተካሂዷል። በጥያቄና መልሱ የተካፈሉ ሴት ተማሪዎች በመቶኛ ስንተ ናቸው?

ሀ. 6% ለ. 40% ሐ. 1.5% መ. 60%

19. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ሁሉም የ39 አካፋዮች 1 ፣ 3 ፣13 እና 39

ለ. ሁሉም የ21 አካፋዮች 1፣3፣7 እና 21

ሐ. ሁሉም የ31 አካፋዮች 1 እና 31

መ.ሁሉም የ68 አካፋዮች 1፣2፣34 እና 68

20. ከሚከተሉት ውስጥ አንፃራዊ ብቸኛ ቁጥር ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. 5 እና 20 ለ. 17 እና 30 ሐ. 28 እና 33 መ. 3 እና 40

21. 28% ወደ ክፍልፋይ ሲቀየር ስንት ይሆናል?

ሀ. $\frac{28}{10}$ ለ. $\frac{114}{500}$ ሐ. $\frac{7}{25}$ መ. $\frac{56}{100}$

22. የሙሉ ቁጥር 13 ከመጀመሪያ አራት ብዜቶች ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?

ሀ. 26 ለ. 65 ሐ. 13 መ. 39

23. ከሚከተሉት ክፍልፋዮች ውስጥ ወደ አስርዮሽ ቁጥር ሲለወጥ ኢ-አክታሚ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. $\frac{7}{13}$ ለ. $\frac{9}{8}$ ሐ. $2\frac{1}{4}$ መ. $\frac{3}{5}$

24. ትጋብ (ሀ፣ለ) = 75 የሆነው ከሚከተሉት ውስጥ የ'ሀ' እና 'ለ' ዋጋ የቱን ሲሆን ነው?

ሀ. 3 እና 25 ለ. 5 እና 15 ሐ. 5 እና 25 መ. 30 እና 25

25. $\frac{3}{4}$ ፣50%፣$\frac{2}{5}$ ፣0.8 ከሚሉት ቁጥሮች ውስጥ ትልቁ የቱ ነው?

ሀ. 50% ለ. $\frac{2}{5}$ ሐ. 0.8 መ. $\frac{3}{4}$



LIVEWORKSHEETS

26. ከ2 እስከ 8 የሚገኙ ብቸኛ ቁጥሮች ትጋብ ስንት ነው?

ሀ. 105 ለ. 30 ሐ. 210 መ. 420

27. ከሚከተሉት ውስጥ ለ $\frac{24}{32}$ ተመጣጣኝ ክፍልፋይ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. $\frac{3}{4}$ ለ. $\frac{12}{16}$ ሐ. $\frac{6}{8}$ መ. $\frac{4}{3}$

28. $\frac{15}{6}$ - 0.42 =______

ሀ. 2.8 ለ. $\frac{52}{25}$ ሐ. 1.44 መ. $\frac{208}{6}$

29. ከሚከተሉት ውስጥ ከ $\frac{5}{4}$ ጋር እኩል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. 1.25 ለ. 120% ሐ. 1 $\frac{1}{4}$ መ. 75%

30. የ600፧ 40% ስንት ነው?

ሀ. 24 ለ. 300 ሐ. 60 መ. 240



LIVEWORKSHEETS